# በኦሮሚያ ክልል የፈንታሌ ወረዳ ነዋሪዎች በጎርፍ ተጠቃን ይላሉ፣

በኦሮሚያ ክልል ፈንታሌ ወረዳ ጎርፍ መከሰቱን የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡ በአካባቢው የሚገኝ የሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት ክፉኛ በጎርፍ መመታቱን ቦሩ ሮባ የተባሉ የፈንታሌ ወረዳ ነዋሪ ለቮኦኤ ገልጸዋል፡

“የደረሰው ጉዳት በጣም ከባድ ነው፡ ጉዲና ቱምሳ GTS የተባለ ሃይስኩል (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) አለ፡ ያን ትምህርት ቤት እንዳለ ወስዶታል (ጎርፍ)” ብለዋል አቶ ቦሩ ሮባ፡

የምስራቅ ሸዋ ዞን መስተዳድር በበኩሉ መጠነኛ ጎርፍ በመተሃራ ከተማ አቅራቢያ እንደነበረና ያስከተልው ከፍተኛ ጉዳት እንደሌለ ለቪኦኤ አብራርቷል፡

የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ አብራሃም አዱላ ጉዳቱ መጠነኛ ነው ብለዋል፡

“የፈንታሌ ወረዳ ዋና ከተማ በሆነችው መተሃራ አቅራቢያ በሰቃ ሀይቅ የሚባል የተፈጥሮ ሃይቅ አለ፡ በበጋው ወር ውስጥም አልፎ አልፎ ዝናብ ይዘንብ ስለነበረ፣ መጀመሪያ ካለው የውሃ ይዘቱ የጨመረበት ሁኔታ አለ፣” ብለዋል፡

በመተሃራ የስኳር ፋብሪካና በግል የከብት ማደለቢያ አካባቢ የተወሰነ ጥፋት መድረሱንና የሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት በጎርፍ መጥለቅለቁን የተናገሩት አቶ አብርሃም አዱላ፣ በሰው ላይ የደረሰ ጉዳት አለመኖሩን አረጋግጠዋል፡

ባለፈው ሳምንት በአማራ ክልል አከታትሎ የጣለው ዝናብ በአምስት ወረዳዎች 37 ሰዎችን ሲገድል ከ6ሽህ በላይ ሰዎችን ማፈናቀሉን የክልሉ ባለስልጣናት አስታውቀዋል፡

በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የአስቸኳይ ጊዜ ሰራተኞች የተጎጂዎቹ ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል በመግለጽ ላይ ናቸው፡

የክረምቱ ዝናብ እስከ ጥቅምት ወር ድረስ ሊቀጥል እንደሚችል የኢትዮጵያ ሚቲዮሮሎጂ ድርጅት አስታውቋል፡

# በአማራ ክልል ከጎርፍና ከመሬት መንሸራተት ጋር በተያያዘ የሞቱት ሰዎች ቁጥር 37 ደረሰ

በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን በሃብሩ ወረዳ።በግዳን።ዋድላና በራያና ቆቦ ወርዳዎች።በሰሜን ሸዋ ዞን።በደቡብ ወሎና በተለያዩ አካባቢዎች ጎርፍና የመሬት መንሸራተት በሰው ሕይህወት።በከብቶችና በሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡

አከታትሎ በመጣል ላይ ያለው ዝናብ በአምስት ወረዳዎች 37 ሰዎችን ሲገድል ከ6ሽህ በላይ ሰዎችን ማፈናቀሉን የአማራ ክልል ባለስልጣን አስታወቁ፡

የክልሉ ቃል አቀባይ አቶ ታምራት ደጀኔ ለቪኦኤ ሲናገሩ፡-“አጠቃላይ አደጋው የደረሰው አንደኛ በጎርፍ ጋር በተያያዘ ነው፣ ሁለተኛ ተራራ መንሸራተት ጋር ተያይዞ እዚያ አካባቢ የሰፈረው ሰው ላይ የተናደበትና ህይወቱን ያጣበት… ሁኔታ ነው” ብለዋል፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዜና ምንጭ በጎርፍ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን ሰዎች ቁጥር ከ8ሽህ በላይ አድርሶታል፡

የአስቸኳይ ጊዜ የእርዳታ ሰራተኞች ለተጎጂዎች የጊዚያዊ የምግብ።የመጠለያና የመሰረታዊ የንጽህና መጠበቂያዎችን እያከፋፈሉ እንደሆነ አቶ ታምራት ገልጸዋል፡

“በአካባቢው የሚገኙ የመንግስት አዳራሾች።ትምህርት ቤቶች።አንዲሁም ድንኳን በማቅረብ ሰው እንዲጠለል ተደርጓል፡”